

# በአማራ ህዛራዊ ክልላዊ መንግስት የባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

## በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን የጮቄና አካባቢው ጥብቅ ስፍራ የመሆን የመጀመሪያ ደረጃ የአቅም ጥናት





ግንቦት 2004
ባህርዳር

## ማውጫ


1. መግቢያ ..... 1

2. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 2

3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ ..... 3

3.1 መገኛና ስፋት ..... 3

3.2 የአየር ንብረት ..... 3

3.3 የመሬት አቀማመጥ ..... 4

4. የጥናቱ ዓላማ ..... 4

4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ..... 4

5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች ..... 5

5. 1 ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ማስፈፀሚያ ስልቶች ..... 5

5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች ..... 5

5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ..... 6

6. የጥናቱ ሂደትና የተዳሰሱ አካባቢዎች ..... 6

7. ከዳሰሳ ጥናቱ የተገኙ ውጤቶች ..... 11

7.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ ..... 11

7.2 የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ ..... 11

7.3 የዱር እንስሳት ..... 12

7.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት ..... 13

7.5 የቱሪዝም አቅም ፣ ..... 13

7.5.1 ለቱሪዝም ገበያ የመቅረብ አቅሙ ፣ ..... 14

7.5.2 ለክልሉ የቱሪዝም እድገትና ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦ ፣ ..... 14

8. የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ፣ ..... 20

8.1 የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እና የኑሮ ሁኔታ ፣ ..... 20

9. በጮቄ አካባቢ ያሉ ማህበራት እንቅስቅሴ ..... 22

10. በጮቄ ተራራ የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች ፣ ..... 22

11. የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ ..... 25

12. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ..... 27

13. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና ..... 30

14. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ..... 34

15. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች ..... 35
16. የጉዳዩ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና ..... 36
17. ዋቢ መጽሐፍት (References) ..... 43
ዕዝል 1 ዋና ዋና የእዕዋት ዝርያዎች ..... 44
ዕዝል 2 አጥቢ የዱር እንስሳት ..... 47
ዕዝል 3 ዋና ዋና የአዕዋፍ ዝርያዎች ..... 48
ዕዝል 4 ዋና ዋና የጅኪኤስ መረጃዎች ..... 50
ዕዝል5 በጮቄ አናት የሚገኙ ህገወጥ የሰፈራ ና የእርሻ መስፋፋት እንቅስቃሴዎች ..... 54
ዕዝል6 በጮቄ ዙርያ ወረዳዎች የተቋቋሙ የተፈጥሮ ሃብት እና ቱሪዝም ልማት ማህበራት ዝርዝር ..... 56
ዕዝል7 ከጮቄ የሚነሱ የአባይ ገባር ዋናዋና ወንዞች ..... 57
ዕዝል8 የቤት እንስሳት መረጃ ..... 59
ዕዝል9 የህዝብ ብዛት/የ2002 ዓ.ም. ህዝብ እና ቤቶች ቆጠራ/ ..... 62

## 1. መግቢያ

በክልሉ የሚገኙ በርካታ የደን ክልሎች ለረጅም ዓመታት በሰዎች ተፅዕኖ ውስጥ ሆነው ቆይተዋል፡፡ መሬቱና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሐብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 3 ብሄራዊ ፓርኮች ያሉ ሲሆን ይህም በIUCN መስፈርት መሰረት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 10 ከመቶ መሸፈን ያለበት ቢሆንም እነዚህ ጥብቅ ስፍራዎች ከጠቅላላ የክልሉ ቆዳ ስፋት የሚሸፍኑት 2 ከመቶ ብቻ ነው፡፡

ቢሮው በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያላቸውን ቦታዎች በማጥናትና በመከለል ህጋዊ ከለላ እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች ከጣና ሐይቅ በስተደቡብ የሚገኘውን የጮቄ ተራራና አካባበውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ የፖቴንሽያል ጥናት ማካሄድ ቢሮው በያዘው ዕቅድ መሰረት የጥናት ስራውን አከናውኗል፡፡ የጮቄ ተራራ ሰንሰለቶች በዋናነት የሰብ አፍሮአልፓይን እና አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳሮች (Sub afroalpine and Afroalpine Ecosystems) ይዘው የሚገኙ ሲሆን ይህ ሥርዓተምህዳር ከ3200 ሜ ከፍታ በላይ ሲሆን የሃገራችህን ሰንሰለታማ ተራራዎች የሚያካልል ነው፡፡ አገራችን በአፍሪካ ከሚገኙ ተመሳሳይ ስርዓተምህዳሮች 80% ይዛ ትገኛለች፡፡ ይህ ስርዓተምህዳር በዙሪያው ከሚገኙ ዝቅተኛ ስፍራዎች በጣም የተለየና እንደደሴት በመሆን ብርቅየና ድንቅየ የዱር እንስሳትንና ዕፅዋትን አቅፎ ይይዛል፡፡ በአገራችን ይህ ስርዓተምህዳር በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ፣በስሜን ተራራዎች ብሄራዊፓርክና በቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርኮች እየተጠበቀ ሲሆን በመንዝ ጓሳ መጠበቅ እንዲችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን የጮቄ አካባቢ ወደማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት መሸጋገር በአገሪቱ ያለውን የአፍሮ አልፓይን የጥበቃ ሽፋን ከፍ ያደረገዋል፡፡ በጮቄ አካባቢ ከ85 በላይ የእጽዋት አይነቶች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ መካከል ጅባራ፣ ግምይ፣ ጓሳ፣ አስታ፣ ቅርቅሃ፣አሸንግድዬ ጥቂቶች ናቸው፡፡ የጮቄ አካባቢ የአባይ ወንዝ የውሃ ምንጭ ሲሆን የአባይ ተፋሰስ የውሃ ማማ እንደሆነ ይታመናል ከአባይ ተፋሰስም 9.5% ተፋሰስ ደርሻ አለው፡፡ በአጠቃላይ የአባይ ገባር የሆኑ ከ23 በላይ ለሚሆኑ ትላልቅ ወንዞች መፍለቂያ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 16 የአዕዋፍት ዝርያዎች በጮቄ ውስጥና በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህ ሌላ በሀገራችን ከሚገኙ በዓለም አለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት የተቃረቡ (Globally threatened) 31 ዝርያዎች ውስጥ አንዱ Abyssinian Longclaw (*Macronyx flavicollis*) በዚሁ አካባቢ ተጠልሎ ይገኝል፡፡ በአካባቢው በ1995 እ.ኤ.አ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት 49 ያህል የአእዋፋት ዝርዎች እንደሚገኙ ያመለከተ ሲሆን በዚህ የዳሰሳ ጥናትም 41 የወፍ ዝርያዎች ተመዝግበዋል ። በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር ጮቄና አካባቢው በአይ ቢ ኤ መስፈርት (IBA Criteria) መሰረት ኤ ደረጃ 1 እና 3 (A1 and A3 Category) እንደሚያሟላ የታወቀ ሲሆን በዚህ ጥናትም የጮቄ  የተራራ ሰንሰለቶች የሚመለከታቸው አጋር አካላት ና አካባቢው ህብረተሰብ ጋር በአካባቢው ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ ከሰሩና ዳር ድንበሩን ከልሎ ማልማት ፣መጠበቅና መጠቀም ከተቻለ የማህበረሰብ  ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ሲኖረው ችግሮችን መፍታት ካልተቻለ ግን ወደ ጥብቅ ስፍራነት ማሸጋገር አስቸጋሪ ነው፡፡

## 2. የጥናቱ አስፈላጊነት

- በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር ከ4 ወደ 11 በመጨመር በክልሉ የሚገኘውን ወሳይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር ማሳደግ በማስፈለጉ፣
- የአካባቢው ስርዓተ ምህዳሮች (Sub afroalpine and Afroalpine Ecosystems) በእርሻ መስፋፋት፣ በልቅ ግጦሽ እና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ችግር የሚደርስበት በመሆኑ የችግሩን መነሻና መፍትሄ ለማፈላለግ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ፣
- በውስጡ የሚገኘውን ብዝሃ ህይወት ሃብት አቅም ለማወቅ ፣
- የተፈጥሮ አካባቢውን  አካባባዊ፣ ኢኮኖማያዊ፣ ባህላዊ እና የቱሪዝም ጠቀሜታ አቅም ለማወቅ ፣

## 3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ

### 3.1 መገኛና ስፋት

የጮቄ ተራራዎች በምስራቅ ጎጃምና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች በ9 ወረዳዎች ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ጠቅላላ ስፋቱም ወደ 53358 ሄ/ር እንደሚደርስ በአካባቢው የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ አካባቢው /የጮቄ አካባቢ/ በደቡብ ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በጎጃም አካባቢ ከፍተኛው ተራራ የሚገኘው ከዚሁ ተፋሰስ ውስጥ ነው፡፡ ጮቄ ከደብረማርቆስ ከተማ በስተስሜን ምስራቅ አቅጣጫ 38 ኪ.ሜ ላይ የሚገኝ ሲሆን የስናን ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ሮቡ ገበያ ደግሞ በ11 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጮቄን አካባቢ ከደብረማርቆስ ድጎ ጂዎን ሞጣ የሚሄደው አንደኛ ደረጃ የጠጠር መኪና መንገድ እንዲሁም ከድጎጂዎን ፈረስቤት፤ ከደብረማርቆስ ቁይ ቢቸና የሚያገናኙ አውራ መንገዶች የሚያቁርጡት በመሆኑ ጮቄን ለመጎብኘት መንገድ ችግር አይሆንም በተለይም ከደብረማርቆስ ድጎጂዎን ያለው አውራ መንገድ የአካባቢውን ከፍተኛ ቦታዎች አቋርጦ ስለሚሄድ ቦታውን ለመጎብኘት እንደ አንድ እድል ሊወሰድ ይችላል፡፡ አካባበው በግምት በ$10^0$42.00' ሰሜን ላቲቲዩድና በ$372^0$52.00' ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታም ከ2800 እስከ 4088 ሜትር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የጮቄ አካባቢ በስተምስራቅ ከእነማይና እናርጂና እናውጋ ወረዳዎች፤ በስተሰሜን ምስራቅ ከሁለት እጁ እነሴ ፤በስተስሜን ከቢቡኝ፤በምዕራብ ከማቻከል ፤በስተደቡብ ከስናን እንዲሁም በስተ ደቡብ ምስራቅ ከድባይ ጥላት ግን ወረዳዎች ይዋሰናል፡፡

### 3.2 የአየር ንብረት

የጮቄ አካባቢ የአፍሮ አልፓይንና ሳብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተምህዳርን ይ ወክላል፡፡

በአካባቢው የሜትሮሎጂ ጣቢያ ባለመኖሩ በትክክል የተወሰደ የዝናብና የሙቀት መጠን መረጃ ባይኖርም ከአካባቢው የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአካባቢው የዝናብ መጠን ከ900-1400 ሚ.ሚ የሚደርስ ሲሆን የአካባቢውን አማካይ የሙቀት መጠን በተመለከተ ደግሞ ወደ $0^oc$ አካባቢ እንደሚደርስ መረጃዎች ሲያስረዱ በክረምት ወቅት ከሳምንት ለማይበልጥ ጊዜ በበረዶ ይሸፈናል፡፡ በጮቄ የላይኛው አካባቢ ለወራት አካባቢው ውርጭ /Frost/ ስለሚሆንና ከአፈር የሚገኘው እርጥበት በተክሎች ስር ለመሳብ ስለሚያስቸግር ለተክሎች እድገት ምቹ አይደለም፡፡

### 3.3 የመሬት አቀማመጥ

የጮቄ አካባቢ የመሬት አቀማመጥ 86 ከመቶ ተራራማ፣ 1.5 ከመቶ ሸለቆማና 12.5 ከመቶ ሜዳማ እንደሆነ ከአካባቢው የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ ።

የጮቄ አካባቢን ሰንመለከተ የተፋሰሱ የታችኛው ክፍል ማለትም የአቢያ ወንዝንና መሰል አካባቢዎችን ተከትሎ ሸለቋማ ሲሆን በዚህ አካባቢ እንደ ሾላ፣ሎል፣ክትክታ ግራር፣ቅላቦና አምቡስ በመሳሰሉ እጽዋት የተሸፈነ ነው። የጮቄ የመካከለኛው ክፍል ተራራማና ተዳፋታማ ሲሆን ይህ አካባቢ በዋናነት በአስታ ተሸፈነ ሲሆን አልፎ አልፎ የአምጃና በሌሎች እጽዋት የተሸፈነ ነው ከዚህ በተጨማሪ የጮቄ የላይኛው አካል በአብዛኛው ሜዳማ ሲሆን ይህም በጂባራ፣ግምይና አሸንግድየ ተክሎች የተሸፈነ እና አካባቢው ከፍተኛ የሆነ የግጦሽ ጫና አለበት።



የጮቄ ተፋሰስ የላይኛው ክፍል

### 4. የጥናቱ ዓላማ

በምስራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ የሚገኘውን የጮቄ ተራራዎች አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳሮች የብዝሃ ህይወት ሃብት እና የተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች አቅም የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የአካባቢውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ማደራጀት፣

### 4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- የጮቄ ተራራዎችን የብዝሃ- ህይወት ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣
- የጮቄ ተራራዎችን የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸውን አቅም ማጥናት፣

- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት ወደፊት አካባቢው ወደ ጥብቅ ስፍራነት ሊመጣ የሚችልበት ዕድል ካለ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች

### 5. 1 ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የሚመለከታቸውን አጋር አካላት በመያዝ (አስተዳደር፣ ግብርናና ገጠር ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝም፣ አካባቢውን በደንብ የሚያውቁ ግለሰቦች) የጮቄ ተራራዎችና አካባቢው ውስጥ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋትና ኢኮሲስተም እና የአካባቢው ብዝሃ ህይወት ሃብት ይዘት ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል፣

- የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተምና የሶሽዮ.ኢኮኖሚ ጥናት ለማካሄድ የጥናት መስመሮችን ተጠቅመናል፣

- የሚመለከታቸውን የዞንና የወረዳ መ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማነጋገር ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል ፣

- በአካባቢው ላይ ከአሁን በፊት የተሰበሰቡና የተጠኑ መረጃዎችን ተጠቅመናል፣

- ስለጮቄ የተዘጋጁ መረጃዎችን ከኢንተርኔትና ሌላ የመረጃ ምንጮችን ጥቅም ላይ አውለናል

- ዕፅዋት፣ ታላላቅ አጥቢዎችንና አዕዋፍን ለመለየት ጋይዶችን ተጠቅመናል

### 5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

- ጂፒኤስ.....1
- ባይኖኩላር.....1
- ዲጂታል ፎቶ ካሜራ.....1
- ቶፖ ሸት.....የጮቄ አካባቢ ቶፖሸቶች)
- ጋይድ ቡክ.....(የአእዋፋት፣ የአጥቢዎችና የዕፅዋት ማረጋገጫ መጽሐፍት)

### 5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በወረዳና በዞን ደረጃ በጮቄ ተራራዎችና አካባቢው የተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣
- በወረዳና በዞን ደረጃ በጮቄ ተራራዎች እና አካባቢው ለቱሪዝም ምቹ የሆኑ ባህላዊና ተፈጥሮዊ ቅርሶች ተለይተዋል፣
- በወረዳና በዞን ደረጃ በጮቄ ተራራዎች እና አካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትን፣ ዕፅዋትን፣ ሥርዓተ-ምህዳርና የሶሽዮ-.ኢኮኖሚ ሃብቶች መረጃ ተሰብስቧል፣
- ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን በጮቄ አካባቢ ያለው አጠቃላይ መረጃ ተሰብስቧል ፣
- የቱሪስት መመልከቻ ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎች ተለይተዋል
- ከጮቄ የሚነሱ ዋና ዋና ወንዞች ተለይተዋል
- በአካባቢው ላይ እየደረሱ ያሉ ዋና ዋና ተጽዕኖዎች ተለይተዋል

### 6. የጥናቱ ሂደትና የተዳሰሱ አካባቢዎች

ደብማርቆስ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን ጮቄን የሚያዋስኑ 9 ወረዳዎችን የለየን ሲሆን ከየትኛው ወረዳ በመጀመር ሁሉንም ወረዳዎች ማየት እንደምንችል በዝርዝር የተወያየን ሲሆን የጥናታችንም ቅደም ተከተል ከስናን ወረዳ በመጀመር ወደ ቢቡኝ ወረዳ ከቢቡኝ ወረዳ ወደ ደጋ ዳሞት ወረዳ አንደገና ቢቡኝ በመመለስ ወደ ድባይ ጥላት ግን ወረዳ አንድንሰራ ከድባይ በመነሳት እነማይ ከዚያም እናርጂ እናውጋ ከዚያ ወደ ሁለት እጁ አነሴ ከዚያም በመነሳት የአዋበልን ወረዳ በመስራት የማቸከል ወረዳን መረጃን መሰብሰብ የምንችል መሆኑን ከተማመንን በኋላ የጉዞ መስመሮችን በየወረዳዎች በመሆን ወስነን ሰርተናል፡፡ በጉዞ ወቅት የተከተልናቸው የጉዞ መስመሮችም የሚከተሉት ናቸቸው፡፡

- ከስናን ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ሮቡ ገበያ በመነሳት በጠጠር አራት መከራክር ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብት ና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line one/

- በዚህ የጉዞ መስመር የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችና መገለጫቸው፡
  - ✓ ከረቡዕ ገበያ ጮቄ መግቢያ ይህ ቦታ የሚገኘው ከሮቡ ገበያ 10 ኪ.ሜ /X=369580 y=1171487/ ሲሆን ጮቄን ለመጎብኘት በቅርብ ለመጎብኘት የሚያስችል ቦታነው፡፡
  - ✓ የአባ ጂሜ ደን በአባዛኸር ቀበሌ ውስጥ የመገኛ ቦታው/ x=372235 y=1175794/ ሲሆን ጥቅጥቅ ባለ የአስታ ደን የተሸፈነ ሲሆን አካባቢው በአስታ ቀለበት ክልል ውስጥ የሚበቅሉ አጽዋትን ለመመልከት ወሳይ የሆነ አካባቢ ሲሆን ተፈጥሯዊነቱ እንደተጠበቀ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ከእጽዋት አስታ ፣ኩሸሽላ፣ነጫቴና ጂባራ በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን ከዱር እንስሳት ውስጥ የዱር አሳማ ፣ዝንጀሮና ተራ ቀበሮ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡
  - ✓ ከጠጠር አናት አንባ በተንዝንበት ወቅት አካባቢው ከፍተኛ የሆነ የእንስሳት ጫና ያለበት መሆኑንና ከፍተኛ የሆነ የቤት እንስሳት ስምሪት መኖሩን የተገነዘብን ሲሆን ይህ አካባቢ በዋናነት የሚገኙት እጽዋት ግምይ፣አሸንግድየና ጀባራ ናቸው ፡፡ አራት መከራክር በመባል የሚታወቁት /እናት አንባ ፤ገማሴ አንባ፣ቁሊጥ አንባና ሌማት አንባ/ ሲሆኑ በዋናነት እናት አንባ አቅፎ በያዛቸው መስህብ ሃብቶች የተፈጥሮ ዋሻ ዋሻ፣የመከራክር መድሃኒያለም ቤተክርስቲያንና የተለያዩ ዕጽዋትና የዱር እንስሳትን አቅፎ የያዘ ሲሆን በተለይ ከአካባቢው ከፍ ያለ በመሆኑ ወደ ስናንና ማቻከል ወረዳዎች ያሉ ማራኪ ገጽታዎችን ለመመልከት በመመልከቻ ቦታነት ሊያገለግል ይችላል፡፡የእናት መከራክር መገኛም /x=364848 y=1175197/ ነው፡፡

- 👍 ከጠጠር በፈልፈል ሜዳ ዋብር እስከ ሞላላ ዋሻ ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብት ና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line Two/
  - ✓ ከጠጠር ወደ ድጎ ጺዎን ሲጓዙ ግምይና ጂባራ የበዛበትን ደልዳላ መሬት አልፍን የምናገኘው የፍልፈል ሜዳ/x= 373421 y= 1184115/ ከፍተኛ ቦታን እናገኛለን፡፡ ይህ ቦታ ከፍታው ከባህር ወለል 4088 ሜ ሲሆን የጮቄ ክፍተኛ ቦታ የሚገኘው እዚህ ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ለቱሪስት ማረፊያነት ማገልገል የሚችል ሲሆን የአካባቢውን ገጽታ ለመመልከት በመመልከቻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ አካባቢ ያለው የፍልፈልና የአይጥ ብዛት ቀይ ቀበሮን ወደ አካባቢው ማምጣት ቢቻል ማላመድ የሚቻልበት እድል መኖሩን ያመላክታል፡፡
  - ✓ ከፍልፈል ሜዳ ወደ ዋብር ከተማ ስንሄድ በመሃል ከፍተኛ የሆነ ጂባራ ያለበት ቦታ አለ ይህም የአፍሮ አልፓይን መገለጫ ነው፡፡ ከዚህ ቦታ በመነሳት ወደ ሰማይ ላስ

መሄድ ይቻላል። ዋብር መንደር በፊት መንደር ሳይኖረው ለገበያ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን አሁን ግን ወደቋሚ መንደርነት ብሎም ወደከተማነት በመለወጥ የጮቄ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚችለውን ቦታ ይቆርጠዋል።

- ✓ ከዋብር በመቀጠል እናት ዋብርን / x=367381 y=1186219/ አናገኛለን ይህ ቦታ ወደ አቢያ ሸለቆና ወደ ሞላሌ ዋሻ እንዲሁም የዝምብል ወንዝን ተከትሎ ወደ ደንበጫ ለመመልከቻነት ሊያገለግል ይችላል። ይህ ቦታ ከሌላዎች በተለየ ከፍተኛ የሆነ የአሸንግድየ እጽዋት ይገኝበታል።
- ✓ ከእናት ዋብር እስከ ሞላሌ ዋሻ ስንጓዝ ሸለቋማ በሆነ መንገድ የተጓዝን ሲሆን ከ1902 ዓ.ም ጀምሮ ሰው ሲኖርበት የቆየው የሞላሌ ዋሻ/ x=365500 y=1186796/ እናገኛለን ።በዚህ ዋሻ ውስጥ አቶ ልቅና አደመ ከአራት ኣመት እድሜያቸው አንስቶ ለ36 አመታት የኖሩበት ሲሆን እሳቸው ዋሻውን በውርስ ያገኙት ከአባታቸው ከአቶ አደመ መርሻ ሲሆን አቶ አደመ መርሻ ደግሞ ከአባታቸው ከአቶ መርሻ ገብሬ ሲሆን አቶ መርሻ ገብሬም የዋሻው የመጀመሪያ ባለቤት ናቸው። የዋሻው ስፋት 200 ሜ$^2$ እንደሚሆን ይገመታል። በአሁኑ ስዓት አባወራውን እስከ ቤተሰባቸውና ቤት እንስሳቸው በዋሻው ውሥጥ ተጠልሎ ይኖራል።



ከ1902 ጀምሮ ሰው እየኖረበት ያለ ዋሻ

- **ቢቡኝ እስከ ፈረስቤት ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line Three/**

ከቢቡኝ ከተማ /x=362008 y=1199064/ በመነሳት ወደፈረስቤት ከተማ ስንሄድ 11 ኪ.ሜ እንደተጓዝን ከድጎ ፅዮን የፈረስ ቤት መገንጠያ /x=363473 y=1190224/ አናገኛለን ከዚህ ቦታ በመነሳት እስከ በረቅ ደን /x=354627 y=1192308/ ያለው ቦታ የጮቄ አካል ሲሆን ሙሉ በሙሉ

ለእረሻና ለግጦሽ አገልግሎት የዋለ በመሆኑ ለጥብቅ ስፍራነት ሊውል የሚችል ቦታ የለውም፡፡ይህም መስመር 11ኪ.ሜ ርዝመት አለው፡፡

- **ከቁይ በእነቁይ እስከ በቅሎ መስበሪያ ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line Four/**


የአባራን በአስታ የተሸፈነ ደን

ከቁይ ከተማ /x=389621 y=1161041/ ወደ በቅሎ መስበሪያ ስንሄድ ጠቅጥቅ ባለ የሃበሻ ጽድ ተሸፈነውን የወደብ እየሱስ ቤተክርስቲያንን እናገኛለን፡፡ ከዚያ በመቀጠል እነቁይ ቀበሌ ያለችውን የገልባጤን መንደር እናገኛለን፡፡ከዚያ በመቀጠል ወደ በቅሎ መስበሪያ ስንሄድ ተዳፋታም የሆነውን የጮቄን አካልና የአባራን በአስታ የተሸፈነ ደን እየተመለከትን የድባይ ጥላትግን፣አነማይ፣እናርጂ እናውጋና የሁለት እጁ እነሴ ወረዳዎች መገኛኛ ሆነውን በቅሎ መስበሪያ አፋፍ /x=384450 y=1182134/ላይ ከፍታ ከባህር ወለል 3935 ሜ ይህ ቦታ ከአንጎታ መንደር አናት ላይ በመሆን ወደጨየ ወንዝና የጮቄን ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ መመልከቻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ከዚህ አካባቢ ግምይ ከሁሉም አካባቢዎች በተለየ ተፈጥረዊነቱን እንደጠበቀ የሚገኝበት ሲሆን ሰፋ ያለ የሳር የጂብራና በሳር ምድር የተሸፈነ ሲሆን የቀይ ቀበሮን ወደ አካባቢው ለማላመድ ጥቅም ላይ ቢያውሉት ግልጋሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

- **ከቢቸና ዲማ እንዲሁም የዋሻ ጊዮርጊስ ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line five/**

ከቢቸና ከተማ /x=412181 y=1154957/ በመነሳት ወደ ደብረወርቅ ስንሄድ 18 ኪ..ሜ እንደተጓዝን የዲማን መገንጠያ /ጠልማ /x=407764 y=1171834/ አናገኛለን ከጠልማ ወደ ምስረቅ አቅጣጫ 10 ኪሜ እንደተጓዝን ታሪካዊውን የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም/x=414572

y=1165955/ እናገኛለን፡፡ በዲማ ጊዮርጊስ የቅኔ፣የዜማ ፣የመጽሃፍና የፊደልና የቁጥር ትምህረት የሚሰጥ ሲሆን በተለይም በመጽሃፍ ማስመስከሪያነቱ ይታወቃል፡፡ ከዚያም በመመለስ ወደዋነው መስመር በመውጣት ከጠልማ በስተምዕራብ 11ኪ..ሜ በመኪና ከዚያ የአንድ ስዓት በእግር እንደተጓዝን ታሪካዊውን በ1100 የተቋቋመውን የዋሻ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን /x=396454 y=1181861/ እናገኛለን ፡፡ የዋሻ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በሃበሻ ጽድ የተሸፈነ ሲሆን በአካባቢው 3 ክፍል ያለው ዋሻ ሲኖር ይህም ዋሻ በጠላት ወረራ ወቅት ለመጠለያነት እንዳገለገለ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡

- **ከግንደወይን ባህረጊዮርጊስ ሃይቅና መርጦለማሪያም ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line six/**

ከግንደወይን ከተማ /x=400124 y=1207596/ በመነሳት ወደ መርጦ ለማሪያም የሚሄደው አውራመንገድ ይዘን እንደተጓዝን ወደሰሜን በመገንጠል 10ኪ..ሜ እንደተጓዝን በክልሉ 4ኛ ደረጃ የያዘውን የባህረ ጊርጊስ ሃይቅ ጎብኝተናል፡፡ ሃይቁ 112 ሄ.ር ስፋትና ከ20-25 ሜ ጥልቀት ሲኖረው በዙሪያው አራት ዋሻዎችና ታላላቅ ዛፎች እንደገተም፣ሎል፣ጥቁር እንጨት፣ሾላና የመሳሰሉ ዛፎች የሚገኙበትና ወደ ሃይቁ የሚገባውን ደለል መከላከል ከተቻለ ሃይቁን በመስህብነት መጠቀም ይቻላል ፡፡ ከዚህም ወደዋናው መስመር በመመለስ ጉዞአችን ወደ መርጦለ ማሪያም /x=420799 y=1200718/ በመሄድ በየጉዲት ጉዲት ጉዳት የደረሰበትን የቤተክርስቲያኑ ፍርስራሽና በዙሪያው ያሉ የመስብ ሃብቶችን ተመልክተናል፡፡

- **ከሞጣ ሰማይ ላስ ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line Seven/**

ከሞጣ ከተማ /x=378190 y=1224643/በመነሳት ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመጓዝ የሰማይ ላስን የተራራ አካበቢ/x=380307 y=1192798/ እናገኛለን ፡፡ የሰማይላስ አካባቢ የጎማ ዱርንና ወደ ስሜን የሁለት እጁ እንሴ ወረዳን መመልከቻ ለመሆን የሚያስችል ሲሆን አካባቢው የሰማይ ላስ መዳህኒያለምንና ሙሽሪት ገደልን በውሰጡ አቅፎ የያዘና አካባቢውን ለመጎብኘት በቀላሉ በእግር ከፍተኛውን ቦታ እየጎበኙ ወደ ደድ ቀበሌ መውጣት ይቻላል፡፡ በዚህ አካባቢ በአካባቢው የሚበቅሉና የአፍሮ አልፓይን የሚወክሉ እጽዋት ይበቅሉበታል፡፡

- **ከደምበጫ ሰነቦ ተክለሃይማኖት ያለውን ቦታ የተፈጥሮ ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን መረጃ መሰብሰብ /Transect line Seven/**

የሰነቦ ተክለሃይማኖትና አካባቢውን መረጃ ለመሰብሰብ መነሻችን ደንበጫ በማድረግ ወደ ፈረስ ቤት 23 ኪ.ሜ በመኪና አንደተጓዙ ሁለት ኪ.ሜ በእግር እንደተጓዙየሰነቦ ተክለሃይማኖትን የዋሻ ገዳም /x=343430 y=1187029/ ይህ ገዳም ታላላቅ የዛፍ ዝርያዎችን አቅፎ የያዘ ከመሆኑ ባሻገር ለብዙ ምዕመናንም የጸበል አገልግሎትን በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የሰነቦ ተክለሃይማኖትና አካባቢውን ለመጎብኘት በሚኬድበት ወቅት እግረመንገዱን የሰቀላ ማሪያምን ደንና የአካባቢውን ማራኪ ገጽታ መመልከት ያስችላል

## 7. ከዳሰሳ ጥናቱ የተገኙ ውጤቶች

### 7.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ

የጮቄ አካባቢ ከ1966 ዓ.ም በፊት ህጋዊ የሆነ የጥበቃ ስርዓት ባይዘረጋለትም የተሻለ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም የተሸለ እንደነበር የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ከደርግ ዘመነመንግስት ጀምሮ በቦታው ላይ ያለው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በተለይም በ1989 ዓ.ም የተደረገው የመሬት ሽግሽግ የተወሰኑ አርሶ አደሮች መሬት ከጮቄው የእረሻ መሬት እንዳገኙ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ ከ1983 ወዲህ ለሌሎች ስርዓተምህዳሮች ጥበቃ ያልተደረገ ቢሆንም በአስታው ቀለበት የደን ጭፍጨፋ እንዳይካሄ በወረዳ ያሉ የግብርና ጽ/ቤቶች ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመነጋገር የአካባቢ ዘበኞች እንዲወከሉ በማድረግ የጥበቃ ጅምር አለ፡፡

### 7.2 የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ




የጮቄ አካባቢ የAfrotropical highland biome እና የአፍሮ አልፓይንና ሳብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን በተፋሰሱ አናት ላይ የሚገኙ ጂባራ ፣ግምይና አሸንግድዬ የመሳሰሉት ዕፅዋትን የሚገኙበት እንዲሁም የአስታውን ቀለበት ተከትሎ በዋናነት የአስታ ሽፋን አለው ። በተጨማሪም የአቢያንና ሌሎች ወንዞችን ተከትሎ ደኖች /rivrine forest / የሚገኝበት አካባቢ ሲሆን Afrotropical highland biome መጠለያቸው

አድረገው የተቀመጡ 16 የአዕዋፍ ዝርያዎችን እና የተለያዩ የአይጥና የፍልፈል ዝርያዎችንም አቅፎ የያዘ አካባቢ ነው።

### 7.3 የዱር እንስሳት

የጮቄ አካባቢ ከአሁን በፊት ብዙ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ተጠልለው እንደቆዩበትና የቀይ ቀበሮ ታሪካዊ የመኖሪያ አካባቢ እንደነበረ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ። ሆኖም ግን አካባቢው እየደረሰበት ባለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት የዱር እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ የዱር እንስሳትን በቀላሉ ማየት አዳጋች ነው። ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከ16 በላይ አጥቢ የዱር እንስሳትና ከ41 በላይ አዕዋፋት፣ ዝርያዎች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት

ከአጥቢ እንስሳት መካከል:-

- ነብር (Leopard)፣
- ተራ ቀበሮ (Common/Golden Jackal)፣
- ተራ ድኩላ (Common bushbuck)፣
- ጉሬዛ (Abyssinian colobus)፣
- ሚዳቋ (Common duiker)፣
- ተራ ጅብ (Spotted Hyena)፣
- ተራ ዝንጅሮ (Anubis baboon)፣
- የዱር ዓሳማ (Bushpig) ጥቂቶቹ ናቸው።

ከአዕዋፋት መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሮ ትሮፒካል ሀይላንድ ባዮም (Afrotropical highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 46 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 16 የአዕዋፍት ዝርያዎች በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ ተረጋግጧል።

Abyssinian Longclaw

Baglafecht Weaver

Brown-rumped seedeater

Dusky Turtle-cove

Erckel's Francilin

Ethiopian Siskin

Moorland chat

Nyanza Swift

Slender-billed starling

Spot-breasted Lapwing

Streaky seedeater

Swainson's sparrow

Tacazze Sunbird

Thick-billed Raven

Wattled Ibis

White-collared pigeon

### 7.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

- **የጮቄ አካባቢ ከ85 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ የተፈጥሮ አካባቢ ነው። ይህ አካባቢ በዋናነት የአፍሮ አልፓይን ስርዓተምህዳር ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን እንደ አስታ፣ጂባራ፣ግምይ ኮሶ ቀጋና ሌሎችም ዕፅዋት የሚገኙበት አካባቢ ሲሆን በተለይም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ**
- *Acanthus sennii*
- *Echinops ellenbeckii*
- *Erythrina brucei*
- *Euryops pinifolius*
- Kniphofia foliosa
- *Lobelia rhynchopetalum*

**አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህን አካባቢ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለጥፋት ተጋላጭ የሆነውን የአፍሮ አልፓይን ስርዓተምህዳር ማልማትና መንከባከብ ነው።**

### 7.5 የቱሪዝም አቅም፣

ጮቄ፣ በክልሉ የጥብቅ ቦታዎች አስተዳደር ስርአት ስር አልምቶ፣ በቱሪዝም እንዱስትሪው ውስጥ ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅሞችን መለየት፣ በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ትኩረት የተሰጠው ስራ ነው። ለዚህ ስኬት፣ የጮቄ ተፈጥሯዊ ቦታ በሀገር ውስጥና አለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ውስጥ ተፎካክሮ፣ ጎብኚዎችን ለመሳብ ምን አይነት ልዩ መስህባዊ ሀብቶችን አሰባስቧል? ለክልሉ የቱሪዝም ልማት ያለው ድርሻ ምን ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚያግዙ ጠቋሚ መረጃዎች ቀጥለው ቀርበዋል።

### 7.5.1 ለቱሪዝም ገበያ የመቅረብ አቅሙ፣

አንድን ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ቅርስ በቱሪዝም እንደስትሪው ውስጥ ለመጠቀም ዋነኛው መሰረት፣ በውስጡ አሰባስቦ የያዛቸው ድንቃ ድንቅ መስህባዊ ሀብቶች ናቸው። ለዚህ ደግሞ፣ ቶማስና ሚድልተን (2003) በአለም አቀፍ ደረጃ ልዩና ድንቅ የሚባሉ የተፈጥሮ እሴት [Exceptional Value] መለያዎችን በዝርዝር አስቀምጠዋል። በዚህ መዘርዝር የጮቄ ተራራዎች፣ በሰዎች ተጽእኖ የብዝሀ ህይወት ኃብትና ተፈጥሯዊ ገጽታቸው የተጎዱ ቢሆንም፣ ለቱሪዝም ገበያ ለመቅረብ የሚያበቃ ውስን አቅም እንዳላቸው ያሳያል።

ከነዚህ አቅሞቹ መካከል፣ የአካባቢው መሬት አቀማመጥና ማራኪ ውበት አንዱ ነው። ስለዚህ፣ የጮቄ ተራሮች ተፈጥሯዊ ገጽታን መልሶ በማልማት፣በመጠበቅ እና ለውበቱ አድናቂና ጎብኚዎች በማስተዋወቅ፤ አካባቢው ከቱሪዝም ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል። በተፈጥሮ ቦታው የአእዋፍ መመልከቻ፣ የተራራና ጉብኝታዊ ጉዞ (Hiking & Trekking ) አገልግሎቶችን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ያመቻል።

ከዚህ ጎን ለጎን፣ የጮቄ ተራሮች እጅግ በርካታ ከሆኑ ምንጮች ውኃ የሚያፈልቁበት ልዩ የተፈጥሮ ቦታ ነው። የአባይ ወንዝ በኢትዮጵያ ድንበር ላይ ለሚኖረው ውኃ ፣ የጮቄ ተፋሰስ ከ10 በመቶ ያላነሰ ድርሻውን አመንጭቶ ያቀርባል።

- በአባይና በገባር ወንዞች ዙሪያ ያለውን ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን ማወቅ የሚጓጉ የተፈጥሮ አድናቂና ጎብኚዎችን፣
- በአባይና ገባር ወንዞች ላይ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምሮች ማድረግ የሚፈልጉ ምሁራንን፣
- ለመማር ማስተማር ሒደት ደጋፊ የሆኑ መግለጫና ማስረጃዎችን ማግኘት የሚፈልጉ ፣ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የትምህርት ተቋማትን

ከሀገር ውስጥና ከተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ወደ አካባቢው በመሳብ ለመጠቀም ያስችላል።

### 7.5.2 ለክልሉ የቱሪዝም እድገትና ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦ፣

የጮቄ ከፍተኛ ቦታዎች በአካባቢው ማህበረሰብ ተጠብቆና ለምቶ ለቱሪዝም ገበያ ቢቀርብ፣ በዙሪያው ከሚገኙ ሌሎች መስህባዊ ኃብቶች ጋር ተሳስሮ፣ ለአካባቢው የቱሪዝም እድገት ግብአት የሚሆን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ለዚህም፣ በጮቄ ተራሮች ዙሪያና የጉዞ መስመር

ውስጥ ያገራችንን ቀደምት የባህል፣ የስልጣኔና ታሪካዊ ሁነቶች ገላጭ የሆኑ በርካታ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡

ከእነዚህ መካከል በጮቄ ተራራ ና በአካባቢው የሚገኙ ዋና ዋና ተፈጥሯዊ፣ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪስት መስህ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድግት ያላቸውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሚከተለው ቀርበዋል ፣

- **የጮቄ ና አራት መከራክር ተራራዎች**




ይህ አካባቢ የአራት ወረዳዎች የጋራ ሃብት ሲሆን በጣም የሚያምርና አእምሮን የሚማርክ አካባቢ ነው ፡፡ የጮቄ አካባቢ በምስራቅ ጎጃም ከሚገኙ ተራራዎች ሁሉ በከፍታው አንደኛ ሲሆን ከፍታውም ከባህር ወለል በላይ 4088 ሜትር ይደርሳል፡፡ የጮቄ ተራራ ሰንሰሎቶች በዋናነት የሰብ አፍሮአልፓይን እና አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳሮች (Afro alpine and Sub afroalpine Ecosystems) ይዘው የሚገኙ ሲሆን በአካባቢው ከሚገኙ ዋና ዋና ዕፅዋቶች መካከል ጅብራ፣ ግምይ፣ ጓሳ፣ አስታ፣ ቅርቅሃ ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓተ ምህዳሮች ዋነኞቹ የአባይ ወንዝ የውሃ ምንጭ ሲሆኑ የአባይ ተፋሰስ የውሃ ማማ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በአጠቃላይ የአባይ ገባር የሆኑ የ23 ትላልቅና የ273 ትናንሽ ወንዞች መፍለቂያ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 16 የአዕዋፍት ዝርያዎች በተራራው ውስጥና በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህ ሌላ በሀገራችን ከሚገኙ በዓለም አለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት የተቃረቡ (Globally threatened) 31 ዝርያዎች ውስጥ አንዱ Abyssinian Longclaw (*Macronyx flavicollis*) ይገኝበታል፡፡ በአካባቢው በ1995 እ.ኤ.አ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት 49 ያህል የአእዋፋት ዝርዎች እንደሚገኙ ያመላክታል፡፡

ይህ የተራራ ሰንሰለት የአራት መከራክር ተራሮች ባለቤት ሲሆን እነዚህ ተራራዎች በስናን ወረዳ ውስጥ በሸዋ ኪዳነምህረት ፣በጠለዛሞና በጣማዊ ቤት ቀበሌዎች መካከል ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተራራዎች ከሰሜን ወደ ምዕራብ ቀጥታ መሥመር ሰርተው የሚገኙና ከፍታቸውም 3583 ሜትር ከባህር ወለል በላይ የሚደርስ ሲሆን ልዩ ከሆነው አቀማመጣቸውና መጠናቸው በተጨማሪ የየራሳቸው ሥም አላቸው፡፡የመጀመሪያው ተራራ **“እናት አምባ”** ሲባል ስያሜውም ትልቅነቱን ለመግለጽ የተሰጠ ነው፡፡ሁለተኛው ተራራ **“ገመሴ አምባ”** ይባላል፤ስሙ እንደሚያመለክተው በተፈጥሮ የተገመሰ ተራራ ነው፡፡ ሶስተኛው ተራራ **“ቁሊጥ አምባ”** ይባላል፤በተፈጥሮ የተቀመጠበት መሬት ከፍ ያለና ተራራው ሞለል ብሎ የወጣ ነው፡፡በስተምዕራብ በኩል የሚገኘው ና አራተኛው ተራራ **“ሌማት አምባ”** በመባል የሚጠራ ሲሆን በተራራው አናት ላይ በእጽዋት የተሞላ ና ሌማት መስል ቅርጽ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

- **ሞላሌ ዋሻ**

በቢቡኝ ወረዳ የሚገኘው የሞላሌ የተፈጥሮ ዋሻ ከዞኑ ዋና ከተማ ከሆነችው ደ/ማርቆስ በሰተሰሜን 60 ኪ.ሜ.ና ከወረዳው ዋና ከተማ ከሆነችው ድጎ ጽዮን በስተደቡብ 20 ኪ..ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ዋሻ ከድጎ ጽዮን ተንሰተን እናት ዋብር ስንደርስ ወደ ምዕራብ በመታጠፍ በእግር 30 ደቂቃ ተጉዘን የምናገኘው ሲሆን ከ1902 ዓ.ም ጀምሮ ሰው ሲኖርበት የቆየው ነው ::

በዚህ ዋሻ ውስጥ አቶ ልቅና አደመ ከአራት ኣመት እድሜያቸው አንስቶ ለ36 አመታት የኖሩበት እና እሳቸው ዋሻውን በውርስ ያገኙት ከአባታቸው ከአቶ አደመ መርሻ ሲሆን አቶ አደመ መርሻ ደግሞ ከአባታቸው ከአቶ መርሻ ገብሬ ሲሆን አቶ መርሻ ገብሬም የዋሻው የመጀመረያ ባለቤት ናቸው፡፡ የዋሻው ስፋት 200 ሜ$^2$ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ በአሁኑ ስዓት አባወራውን እስከ ቤተሰባቸው /ከባለቤታቸው ወ/ሮ ቸኮለች ሞላ ና ሶስት ልጆቻቸው/ና ቤት እንስሳቸው በዋሻው ውሥጥ ተጠልሎ ይኖራሉ፡፡

- **ዲማ ጊዮርጊስ ገዳም**

ዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ከብቸና ወደ ደብረ ወርቅ የሚያስኬደውን አውራ መንገድ አስራ 18 ኪ..ሜ ከተጓዙ በኋላ የዲማን መገንጠያ /ጠልማ / አናገኛለን ከጠልማ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ 10 ኪሜ ገባ ብሎ ይገኛል፡፡ ታሪካዊው የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም የተመሰረተው በ1297 ዓመተ ምሕረት የቀድሞ ስማቸው በኪሞስ በኋላ ግን ተከስተ ብርሃን በተባሉ የሃይማኖት አባት ነው፡፡

የዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ከገናና ረጅም ታሪኩ ጋር አብሮ የዘለቀና በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ ከሚባሉ የቅኔ እና የመጽሓፍት ማስመስከሪያ ትምህርት ቤቶች ውስጥም አንደኛው ማዕከል የአብነት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ገዳሙ በአሁኑ ስዓት ሁሉንም የአብነት ትምህርቶች በስምንት የአብነት መምህራን መድቦ እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን ከእነህም ውስጥ አንደኛዋ ሴት የአብነት መምህርት ለሴቶች ቅኔ በማስተማር ላይ ናቸው፡፡

ከገዳሙ ምስራቃዊ አቅጣጫ ራቅ ብሎ በንግስ ዕለት የሚያከብሩ ፈረሰኞች ፈረስ ማሰሪያ፣ህሙማን የሚፈወሱበት ጸበል ና ዋሻ ጊዮርጊስ የሚባል በተፈጥሮ ደኖች የተሸፈነ ዋሻ እንዲሁም በስተምዕራብ በኩል ያለው ዋሻ ተክለሃይማኖት እንደ ቀለበት በመክበብ ለገዳሙ ከፍተኛ ውበት ሰጥተዉታል፡፡

በዚህ ገዳም ውስጥ ረጅም ዘመናት ያስቆጠሩ ከነገስታት ፣ከመኳንንትና ምዕመናን የተበረከቱ ውድ ታሪካዊ ቅርሶች አሉት ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶችን ለመግለጽ ያህል

- ✓ የአፄ ዮሐንስ 4ኛ የወርቅ ዘውድ ፣የወርቅ መስቀል
- ✓ የአፄ ይስሃቅ የወርቅ ጫማ
- ✓ የእባብ ቅርጽ ያለው የወርቅ ዘንግ
- ✓ የንጉስ ተክለሃይማኖት ጦር
- ✓ ልዩ ልዩ የብራና መጻሕፍት
- ✓ የራስ መኮነን ካባና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

በተለይም ታዋቂው ኢትዮጵዊው ደራሲ ክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ የገዳሙን ሁኔታ በፍቅር እስከ መቃብር መጽሓፋቸው ለኢትዮጵያውያን በስፋት ያስተዋወቁት ሲሆን እርሳቸውም በዚሁ ገዳም ተምረውበታል፡፡

- **ዋሻ ጊዮርጊስ ፍልፍል ቤተክርስቲያን**

ከብቸና ወደ ደብረ ወርቅ በሚያስኬደው አውራ መንገድ አስራ 18 ኪ..ሜ ከተጓዙ በኋላ የዋሻ ጊዮርጊስ ፍልፍል ቤተክርስቲያን መገንጠያ /ጠልማ / አናገኛለን ከጠልማ በስተምዕራብ 11ኪ..ሜ በመኪና ከዚያ የአንድ ስዓት በእግር እንደተጓዝን ታሪካዊውን በ1100 የተቋቋመውን የዋሻ ጊዮርጊስ ፍልፍል ቤተክርስቲያን እናገኛለን ፡፡ የዋሻ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የሚገኝበት ቀበሌ የቀበሃና ሲሆን በቤተክርስቲያኑ ውሰጥ ሰባት/7/ የሚደርሱ ጸበል ቦታዎች አሉት፡፡ የዋሻ

ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በበሃበሻ ጽድ የተሸፈነ ሲሆን በአካባቢው 3 ክፍል ያለው ዋሻ ሲኖር ይህም ዋሻ በጠላት ወረራ ወቅት ለመጠለያነት እንዳገለገለ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ ለዚህም ማሳያ የሚሆነን በ3ኛው የዋሻ ክፍል ውስጥ ለእርሻ መሳሪያነት የሚያገለግለው ቀንበር ፣ከጭቃ የተሰራ ጎታ ና ሌሎች ቁሳቁሶጭ ይገኛሉ፡፡

- **ደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም**

ገዳሟ በእናርጅና እናዉጋ ወረዳ የወረዳው ርዕሰ መዲና እና ራሷ ገዳሟ ለመስፋፋቷ መነሻ ከሆነቻት ደብረወርቅ ከተማ ላይ ትገኛለች፡፡ ገዳሟ ከከተማዋ ዳርቻ ምስራቃዊ አቅጣጫ ክብ ቅርጽ ባለው ኮረብታ ላይ የምትገኝ ሲሆን የገዳሟ ታሪክ እንደሚያስረዳው እስከምትተከል በጊዜያዊ መቃረቢያ ቆይታ የክርስትና እምነት ብሄራዊ በሆነበት አካባቢ በንጉስ አጽበሃ ልጅ በአስፍሃ በ351 ዓ.ም ተተክላለች፡፡ይህች ቤተክርስቲያን በዮዲት ጉዲት በ857 ዓ.ም ተቃጥላ እስከ 1372 ዓ.ም ቆይቶ በዚሁ ጊዜ በአፄ ዳዊት ትእዛዝ በድጋሜ የተሰራች ሲሆን የህንጻ ላይ ቅርጾች ፣ የግድግዳ ሥዕሎች ፣የነገስታት ገጸ-በረከቶች ለገዳሟ ጥንታዊነት ምስክሮች ናቸው፡፡ ቅዱስ ሉቃስ የሳላት ሥዐለ ማርያም /ወይኒቱ/ ፣ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት እና መስቀሎች እንዲሁም ሌሎች ያሏት ሲሆን እነዚህንም ቅርሶች ማስቀመጫ ዘመናዊ ሙዜም ገንብታ ለቱሪዝም እይታ ለማቅረብ የቻለች ገዳም ናት፡፡

- **መርጡለ ማርያም ገዳም**

የመርጡለ ማርያም ገዳም ቤተክርስቲያን በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ዋና ከተማ መርጡለ ማርያም ከባህር ወለል በላይ 2674 ሜትር ከፍታ ባለው ኮረብታማ ቦታ ላይ ትገኛለች፡፡ የመርጡለ ማርያም ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ የኦሪት መስዋዕት ይሰዋባቸው ከነበሩት አምስት አብያተክርስቲያናት/አክሱም ጽዮን፣ጣና ቂርቆስ፣ ተድባበ ማርያም እና ብርብር ማርያም/ ውስጥ አንዷ ስትሆን በቅርስ ሃብት ክምችትም በክልሉ ከሚታወቁት አብያተክርስቲያናት አንዷ ናት፡፡ ገዳሟ በአብርሃና አፅብሃ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሰራ ጥንታዊ የቤተመቅደስ ፍርስራሽ ህንጻ /በዮዲት እና በግራኝ አህመድ ጦርነት ወቅት ጉዳት እንደደረሰበት የሚጠቀሰው/ ፣የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢ የነበረ ድንጋይ ፣የራስ ሃይሉ ውድሞ /የድንጋይ ካብ/ የመሳሰሉ ቋሚ ቅርሶች አሏት፡፡ በተጨማሪም ከ4ኛው መቶ ክ/ዘመን አንስቶ እስከ ዘውዳዊ አገዛዝ መጨረሻ ድረስ ለገዳሟ ከነገስታት የተበረከቱ የነገስታት መጎናጸፊያዎች ና አልባሳት ፣ አክሊሎች ፣የራስ ቁሮች፣ የብራና መጻህፍትና መስቀሎች፣ከብርና ከቀንድ

የተሰሩ ዋንጫዎች፣የአህመድ ግራኝ ነበር የሚባልለት ልብስ ወ.ዘ.ተ መስህቦች አሏት፡፡ በአሁኑ ጊዜ ፈራርሰው ከሚታዩት የህንጻው ግድግዳና አምዶች ላይ የሃረግ፣የአበቦች፣ የመላእክትና የሃዋርያት ምስሎች ይታያሉ፡፡ ሁሉም የረቂቅ ጥበብ ምስክሮች ናቸው፡፡

- **ባህረ-ጊዮርጊስ ሐይቅ**

ከግንደወይን ከተማ በመነሳት ወደ መርጡለ ማርያም የሚሄደው መንገድ ይዘን እንደተጓዝን ወደ ሰሜን በመገንጠል 10ኪ.ሜ እንደተጓዝን በክልሉ ከጣና፣ከሐይቅ እስጢፋኖስ ና አርዲቦ ሐይቆች በመቀጠል 4ኛ ደረጃ የያዘውን የባህረ ጊርጊስ ሐይቅ ያገኛሉ፡፡ ሐይቁ 112 ሄ.ር ስፋትና ከ20-25 ሜ ጥልቀት ሲኖረው በዙሪያው አራት ዋሻዎችና ታላላቅ ዛፎች እንደገተም፣ሎል፣ጥቁር እንጨት፣ሾላና የመሳሰሉ ዛፎች የሚገኙበትና በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ የሐይቁ አፋፍ ላይ ደግሞ ሐይቁ ስያሜውን ያገኘበት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡ ወደ ፊት ወደ ሐይቁ የሚገባውን ደለል መከላከል ከተቻለ ሐይቁን በመስህብነት መጠቀም ይቻላል ፡፡

- **ሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን**

የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ከጥንታዊያን አብያተክርስቲያናት አንዱ ሲሆን በ1751 ዓ.ም. በልዕልት እስራኤል አማካኝነት ተጀምሮ በ1758 እንደተጠናቀቀ ይነገራል ፡፡ የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ከአዲስ አበባ በሞጣ ባህርዳር በሚወስደው መንገድ ላይ ሞጣ ከተማ ውስጥ ከዋናው መንገድ በስተግራ በኩል ትንሽ ገባ ብሎ ይገኛል፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ ከነገስታት ፣ ከመኳንንት እና ከምዕመናን የተበረከቱ ውድና ብርቅ ታሪካዊ መጻህፍት፣መስቀሎች፣ካባዎች ወ.ዘ.ተ.ይገኛሉ፡፡ ረጅም ዘመን ከማስቆጠሩ ጋር በተያያዘ የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ለየት የሚያደርገው የጉልላቱ አሰራር ሲሆን ጉልላቱ የተሰራው አጼ ዮሓንስ በሰጡት ወርቅ አማካኝነት ወርቅ ቅብ እንዲሆን ተደረጎ ነው፡፡

- **ሰነቦ ተ/ሃይማኖት ገዳም**

የሰነቦ ተክለሃይማኖት ገዳም የሚገኘው በምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳድር ደጋዳሞት ወረዳ ሰነቦ ገነተ ማርያም ቀበሌ ሲሆን ከገዳሙ ለመድረስ ከደንበጫ ተነስቶ ወደ ፈረስ ቤት 23 ኪሜ በመኪና አንደተጓዙ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሁለት ኪ.ሜ በእግር በመጓዝ የቀጨም ወንዝ ሸለቆን

ተከትሎ በ1240ዎቹ ዓ.ም በአቡነ ተክለ ሃይማኖት የተመሰረተው ውብ እና ማራኪ ገጽታ ያለው የሰነቦ ተክለሃይማኖት የዋሻ ገዳም ይገኛል። ይህ ገዳም ታላላቅ የዛፍ ዝርያዎችን አቅፎ የያዘ ከመሆኑ ባሻገር ለብዙ ምዕመናንም የጸበል አገልግሎትን በመስጠት ላይ ይገኛል። የሰነቦ ተክለሃይማኖትና አካባቢውን ለመጎብኘት በሚኬድበት ወቅት እግረመንገዱን የሰቀላ ማሪያምን ደንና የአካባቢውን ማራኪ ገጽታ መመልከትም ይቻላል።

## 8. የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ፣

### 8.1 የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እና የኑሮ ሁኔታ፣

የጥናት ቡድኑ በሸፈናቸው በጮቄ ከፍተኛ ቦታዎች /43 ቀበሌዎች/ ሰዎች መኖር የጀመሩበትን ጊዜ ለማወቅ ባይቻልም፣ ከ100 ዓመት በፊት የሰዎች ተጽእኖ በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ መጠነኛ የነበረበት እና በዚህ አካባቢ በርካታ የዱር እንስሳት ዝርያዎችና አእዋፋት ተጠልለው ይኖሩ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ ። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ፣የተፈጥሮ ቦታው በአነስተኛ የሰብል እርሻና እንስሳት እርባታ ጥምር ግብርና በሚተዳደሩ ነዋሪዎች ተፅእኖ ለከፋ አደጋ ተጋልጧል።

በ2002 ዓ.ም በአገርቀፍ ደረጃ በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት፣ በአካባቢው የሚኖሩ አባወራዎች 55,463 ሲሆኑ አጠቃላይ ህዝብ ብዛት ደግሞ 240,847 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 120,088 ወንዶችና 120,759 ሴቶች ናቸው።

ይህ የህዝብ ብዛት ፣ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና መምሪያ ለገጠር ቀበሌዎች በተቀመጠው የ 1.5 የእድገት ስሌት መጠን፣ በ2004ዓ.ም 350,854 እንደሚሆን ይገመታል። ይህን መረጃ፣ የተፈጥሮ ቦታው ካለው አጠቃላይ ስፋት ጋር በማነፃፀር ቢያንስ በ2004ዓ.ም ላይ፡ በ 1 ሄ/ር ቦታ ላይ 1. ቤተሰብ ወይም 6.6 ሰው እንደሚኖር ለመገንዘብ ይቻላል።

ለነዋሪዎቹ የግብርና ስራ የዋለውን የመሬት መጠን የሚገልጽ መረጃ ከየሚመለከታቸው የወረዳ ጽ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ለማግኘት አልተቻለም ። ነገር ግን፣ በጣም ተዳፋታማና ለእርሻ ስራ እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ቦታዎችን ጨምሮ የተፈጥሮ ቦታው አብዛኛው ክፍል በአካባቢው ነዋሪዎች የግብርና ስራ ጥቅም ላይ እንደዋለ ማረጋገጥ ችለናል።

የአካባቢው ነዋሪ በዋናነት የሚያመርተው ለደጋ አየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ የሰብል አይነቶችን ሲሆን ድንች፣ ገብስ፣ስንዴና ባቄላ እንደቅደም ተከተላቸው የአካባቢው ዋነኛ አዝመራዎች ናቸው። በተጨማሪም የአካባቢው ነዋሪ ከሰብል ምርት ስራው ጎን ለጎን የቤት እንስሳትን አርብቶ ይጠቀማል።

ከየወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፣ በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሚገኙት የቤት እንስሳት ከትሮፒክ ከሚረቡ የቤት እንስሳት መጠን [የትቤእመ/TLU] ጋር ሲመዘኑ

150,552.21 እንደሚደርሱ ይገመታል። የቀንድ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ዶሮ ነዋሪው በዋናነት የሚያረባቸው የቤት እንስሳት ናቸው።

ጥቅል መረጃው፣ በጮቄ ከፍተኛ ቦታዎች በሚገኝ 1 ሄክታር መሬት ላይ 2.8 የትቤእመ እንደሚኖር የሚጠቁም ነው። ይህም የአካባቢው ነዋሪ በልቅ ግጦሽ መኖ የሚያረባቸው ቤት እንስሳት በተፈጥሮ ቦታው ላይ የሚፈጥሩትን ከፍተኛ ጫና በቀላሉ የሚያስረዳ ነው።

ይህ ልቅ ግጦሽ፣ ከእርሻና የመኖሪያ መንደሮች መስፋፋት ጋር ተዳምሮ፣ የተፈጥሮ ቦታው የዱር እጽዋትና እንስሳት በዝርያ አይነትና ክምችት በከፍተኛ መጠን ተመናምነው በየቦታው በሚገኙ ትናንሽ ደኖች ውስጥ ተነጣጥለው እንዲኖሩ ምክንያት ሆኗል። የዱር እንስሳቱን ነፃ ዝውውርና የእርስ በርስ ግንኙነትን ገድቧል። የአካባቢውን ተፈጥሯዊ ውበት እንዲመናመን አድርጓል።

ሰንጠረዥ **አንድ** በጮቄ ከፍተኛ ቦታዎች ያለው የቤት እንስሳት ብዛት በትአቤእመ እና በጥናት ወረዳዎችና ቀበሌዎች ገላጭ መረጃ፣

| የጥናቱ | | የቤት እንሰሳው አይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ወረዳ | ቀበሌ ብዛት | የቀንድ ከብት | የጋማ ከብት | በግና ፍየል | ድምር |
| ስናን | 8 | 13,166.15 | 10,484.80 | 3,536.78 | 27,187.73 |
| ቡቢኝ | 7 | 14,260.07 | 4,373.85 | 2,156.59 | 20,790.51 |
| ደባይ ጥላት ግን | 8 | 17,035.17 | 8,915.40 | 2,484.84 | 28,435.41 |
| ሁለት እጅ እነሴ | 7 | 17,684.66 | 9,881.85 | 2,339.09 | 29,905.60 |
| እናርጅ እናውጋ | 4 | 7,718.88 | 2,759.85 | 1,188.14 | 11,666.87 |
| እነማይ | 2 | 3,387.88 | 1,085.25 | 744.64 | 5,217.77 |
| ደጋ ዳሞት | 4 | 10,322.43 | 10,876.55 | 1,944.20 | 23,143.18 |
| ማቻከል | 2 | 2,843.72 | 850.85 | 297.66 | 3,992.23 |
| አዋበል | 1 | 1,336.48 | 567.75 | 309.17 | 2,213.40 |
| ጠቅላላ ድምር | 43.00 | 87,755.44 | 49,796.15 | 15,001.11 | 152,552.70 |

**9. በሙቂ አካባቢ ያሉ ማህበራት እንቅስቅሴ**

በስናን፣ ቡቢኝ፣ ደባይ ጥላት ግን እና ማቻከል ወረዳዎች ህጋዊ እውቅና ያላቸው 22 የተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም ልማት ማህበራት ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ፣ 21ዱ ማህበራት ከተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ባገኙት የገንዘብ ድጋፍ የተለያዩ የተፈጥሮ ኃብት ልማት ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ። የእነዚህ ማህበራት አላማም የአካባቢውን የብዝኃ ህይወት ኃብት መልሶ ማልማት ነው።

ማህበራቱ በዚህ አላማ ስር፣

- የአካባቢውን ነባር የሰብል ዝርያዎች በማራባት፣ በተዘዋዋሪ ብድር ለአባሎቻቸው በማከፋፈል ፣
- የተለያዩ የዛፍ ችግኞችን አፍልቶ በመትከል፣
- የተጎዱ ቦታዎችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ የመጠበቅ ስራዎችን በመከወን ላይ ይገኛሉ።

ሰንጠረዥ **ሁለት** በሙቂ ዙሪያ የተደራጁ የአካባቢ ጥበቃና የቱሪዝም ግብይት ማህበራት ብዛት ፣ የአባላትና የካፒታል መጠን በጥናት ወረዳዎችና ቀበሌዎች ገላጭ መረጃ፣

| ማህበራቱ የሚገኙበት | | የአባላት ብዛት | | | የካፒታል መጠን በብር |
|---|---|---|---|---|---|
| ወረዳ | ቀበሌ ብዛት | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| ስናን | 8 | 2042 | 370 | 2,412 | 2,355,692.05 |
| ቡቢኝ | 5 | 245 | 25 | 270 | 199,523.52 |
| ደባይ ጥላት ግን | 8 | 897 | 398 | 1,295 | 2,272,005.00 |
| ማቻከል | 1 | 27 | 3 | 30 | 600.00 |
| ሪድምር | | 3,211 | 796 | 4,007 | 4,827,820.57 |

**10. በሙቂ ተራራ የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች፣**

- **የህብረተሰቡ ግንዛቤ አናሳ መሆን**




በጮቄ እና አካባቢው የሚገኘው ህዝብ ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ በተጨማሪ የኑሮ ዋስትናውን ያደረገው በጮቄ ተፈጥሮ ሃብት ላይ ነው።ይሁን እንጂ ያለውን ሃብት አሟጦ ከመጠቀም ባለፈ በዘላቂነት የተፈጥሮ ሃብቱ ሳይጎዳ እንዴት መጠቀምና መንከባከብ እንዳለባቸው ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ክፍት በመኖሩ ምክንያት ቦታው/ዋናው የጮቄ ክፍል/ የውሃ ማማነቱን እያጣ ስለሆነ ለታችኛዎች ተፋሰስ አካባቢዎችም ህልውና ስጋት እየፈጠረ ይገኛል። እንዲያውም ከባለሙያዎች ለመረዳት እንደቻልነው በስናን ወረዳ ሸዋ ኪዳነምህረት ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች  የተፈጥሮ ሃብት ስራ አይመለከተንም የማለት እና በቢቡኝ ወረዳ ደብረ ጊዮርጊስ ቀበሌ ደግሞ በወጣቶች የተፈላ 20 መደብ የኮሶ ችግኝ ለተከላ ሲደርስ በጨለማ ማንነቱ ባልታወቀ አካል  በማጭድ ታጭዶ ተከላው ሳይከናወን ቀርቷል። ከዚህ ላይ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር በአንድ በኩል ተፈጥሮ ሃብቱን ያለገደብ አሟጦ መጠቀምን ተግባራዊ ማድረግን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ምንም አይነት ዘላቂ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝ እና እንክብካቤ እንዳይኖር የመፈለግ የአስተሳሰብ ክፍተትን ነው።

- **ሰፊ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር**

በጮቄ እና አካባቢው የሚገኘው ህዝብ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሳት በማረባት የሚተዳደር ሲሆን በተለይም በላይኛው የጮቄ ክፍል በሚገኙ 43 ቀበሌዎች ውሥጥ 41118 በሬ ፣30260 ላም፣13846 ጥጃ፣11,377 ወይፈን፣13382 ጊደር፣29406 ፈረስ፣6951 በቅሎ፣15177 አህያ፣160019 በግ እና 8155 ፍየል በድምሩ 329691 የሚሆኑ የቤት እንስሳት እንደሚገኙ ከግብርና ጽ/ቤቶች የተገኙት መረጃዎች ይገልጻሉ። እነዚህ እንስሳት በአብዛኛው መዋያቸው እና የመኖ ምንጫቸው የውሃ ማማው ጮቄ ተራራ ሲሆን በተለይም በላይኛው የጮቄ ክፍል የሚገኙት ቀበሌዎች ምንም አይነት መኖ ሳያዘጋጁ ዓመቱን ሙሉ በጮቄው ክልል ውስጥ ከአቅም በላይ በማስጋጥ የእንስሳቶቻቸው ሕይወት ተመሰርቷል።

የአካባቢው ማህበረሰብ የሃብት መገለጫ የእንስሳት ቁጥር መሆኑ ደግሞ ሌላው ችግር ነው ይህም  ቁጥርን መሰረት ያደረገው ባህላዊ የእንስሳት እርባታ ዘዴ ጥራት ያላቸው ጥቂት

እንስሳት ተለውጦ ልቅ ግጦሽን ማስቀረት ካልተቻለ በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ የሚያደርሰው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡

- **የደን ጭፍጨፋ እና የደን ቃጠሎ**

በስናን ወረዳ አብአዛኸር ቀበሌ የሚገኘው 68 ሄ/ር የአባ ጅሜ ደን ፣በደባይ ጥላት ግን ወረዳ እነቆይ ቀበሌ የሚገኘው 500 ሄ/ር የአባራ ደን እና በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ የጎማ ዱር ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው 98 ሄ/ር የጎማ ዱር ደን እንዲሁም በሌሎች ቀበሌዎች በተበጣጠሰ መልኩ በሚገኙ ደኖች ውስጥ 85 የሚደርሱ የእጽዋት ዝርያዎችን ለመለየት ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አስታ፣አምጃ ፣ኮሶ ፣ግምይ፣ጅባራ እና የሀበሻ ጽድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብ አስታውንና ግምዩን ለማገዶ ፍጆታ ስለሚጠቀምበት ከፍተኛ ውድመት እየደረሰበት ሲሆን በጥናታችን ወቅት እንደተመለከትነውም እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ የአስታ ጉቶዎች እየተነቀሉ መልሶ እንዳያገግም በማድረግ አንዲሁም በደባይ ጥላት ግን ወረዳ በእንቆይ እና ሸሜ ቀበሌዎች በሁለት ቦታ ላይ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ ከ48 ሄ/ር በላይ የሚሆን የደን መሬት በእሳት ተቃጠሏል፡፡

ያለ ገደብ በሚካሄድ የደን ጭፍጨፋ ምክንያት አካባቢው  በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዳ በመሆኑ ምንጮች እየደረቁ  የውሃው ማማ አናት ላይ የተቀመጡት ሰዎች ለእነርሱና ለከብቶቻቸው የሚሆን ውሃ አጥተው ሲቸገሩ ለማየት ችለናል፡፡

- **ህገወጥ የሰፈራ ና የእርሻ መስፋፋት**

ህገወጥ የሰፈራና የእርሻ መስፋፋት እንቀስቃሴን በተመለከተ  በሁሉም ወረዳዎች የተሟላና የተተነተነ መረጃ ማግኘት ባይቻልም እንኳን በስናን፣ ደባይ ጥላት ግን፣እነማይ ፣እናርጅ አናውጋ፣ቢቡኝና ሁለት እጁ እነሴ ወረዳዎች በተሰበሰቡት መጠነኛ መረጃዎች 248 አ/አደሮች 37.62 ሄ/ር መሬት ላይ ህገ ወጥ የቤት ግንባታ እንዳካሄዱ እና 1176 አባዎራዎች ደግሞ 115.372 ሄ/ር መሬት ላይ ወደ ጮቄው አናት በመውጣት የአስታ ደኖችን በመጨፍጨፍ ለአርሻ ማዋላቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ከጨቄው አናት ሆኖ ለሚመለከተው ሁሉ ከ3500 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ባለው ከፍታ ሰዎች በጣም በተጠጋጋ መልኩ ስፍረው እየኖሩበትና የወል መሬቶችም እስከ ጫፍ ድረስ  ወደ እርሻ ቦታነት በከፍተኛ ፍጥነት እየተቀየሩ ስለሆነ መሬቱ ከሚደርስበት ጫና የተነሳ አፈሩ ውሃ የመያዝ አቅሙ ስለሚዳከም ለህዳሴው ግድብ ዋና ገባር

የሆኑት ከ23 በላይ ወንዞች በዚሁ የመቀጠላቸው ሁኔታ አሳሳቢ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ህብረተሰቡን ባሰተፈ መልኩ የድርሻቸውን በመወጣት አፋጣኝ መፍትሄ ካልተሰጠው የሚያስከትለው ጉዳት በጣም ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

- **የአዋሳኝ ቀበሌዎችና ወረዳዎች ወሰን በትክክል አለመታወቅ**

የላይኛውን የጮቄ ክፍል በዋናነት የሚያዋስኑት ወረዳዎች ስናን፣ ደባይ ጥላት ግን፣ ፣ቢቡኝ ፣እነማይ ና ሁለት እጁ እነሴ ወረዳዎች ሲሆኑ በእነዚህ ወረዳዎች መካከል እና በስራቸው በሚገኙ ቀበሌዎች መካከል ትክክለኛው የድንበር ወሰን ባለመለየቱ ምክንያት እና የተቀናጀ የጥበቃ ስልት ባለመኖሩ የጋራ ወንጋራ እንዲሉ አበው ባለቤት በማጣቱ የተነሳ በአካባቢው የሚኖሩ አ/አደሮች የሃብት ሽሚያ ሰለገጠሙ ያለችውም ሃብት እየወደመች ትገኛለች፡፡ ሰለዚህ አጥር የሌለው ቤት ውስጥ ማንም ዘው ብሎ እንደሚገባ ሁሉ የድንበር ወሰን እና ባለቤት የሌለው የጮቄ ተራራ የተፈጥሮ ሃብትም ማንም እንዳገኘ የሚያወድመው ሃብት በመሆኑ በዚህ ምክንያት እየደረሰ ያለበት ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡

**11. የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ**
**ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ**

- ሰዎች ከተፈጥሮ ሃብቱ በዘላቂነት መጠቀም የሚችሉበትንና ሰዎችና ተፈጥሮ ተጋግዘው በዘላቂነት የሚቀጥሉትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ፡፡
- ለክለት ተጋላጭ የሆነው የከፍተኛ ቦታዎች ሰነምህዳር ለመጠበቅ ያስችላል፡፡
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር፡ያስችላል
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፣
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል (ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ለዓባይ ገባር የሆኑ ከ23 በላይ ዋና ዋና ወንዞች መነሻ በመሆኑ የአባይና ገባር ወንዞች ፍሰት የተስተካከለ እንዲሆን ያስችላል)

**ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ**

- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡
- የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡
- ታላቁ የህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ ስለሚያስችል ደለሉን ለማስወገድ የሚጠይቀውን ወጭ ይቀንሳል
- በሆቴልና አገልግሎት በመስጠት በርካታ ነዋሪዎች ኑሯቸዉን ማሻሻል ይችላሉ

**ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ**

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች የተፈጥሮ ሃብቱን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ዘላቂ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ያስችላል፡፡

**መ/ሳይንሳዊ ጠቀሜታ**

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል በተለይም የደብረማርቆስና የባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች በቅርብ ርቀት ስለሚገኙ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል፡፡
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ ያስችላል፡፡

**ሠ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ**

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል፡፡ በዉስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፣ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸዉ ቆይተዉ ዘለቂታ ባለዉ መልክ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸዉ እንዳይጓደል ይረዳል፡፡
- በጮቄ ተፋሰስ የላይኛው ክፍል ያለው የአስታ ቀለበት ተጠብቆ ሳይጠፋ እንዲቆይ ያስችላል

**ሠ/ የመስህብነት ጠቀሜታ**

- አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ ማራኪ ገጽታወች የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ሰፋ ያለ የአስታ ደን ሽፋንን ለማየት ለሚፈልጉ ጎብኝዎች ለማስተናገድ የሚያስችል ቦታ በመሆኑና በእድሜ ጠገብ አብያተ-ክርስቲያናትና ሌሎች ባህላዊ ቅርሶች የተከበበ ስለሆነ የመስህብነት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል፡፡

**12. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች**

**ሀ/ ወካይነት /representativeness/**

- ቦታው የአፍሮ ትሮፒካል ሃይላንድ ባዮምን በስርዓተ ምህዳር ደረጃም የአፍሮ አልፓይንና ሳብ አፍሮ አልፓይን ስረዓተምህዳር የሚወክል ስለሆነ በማህበረሰብ በጥብቅ ስፍራነት ቢከለል በደቡብ ምዕራብ የልማት ቀጠና ወካይ የሆነ የጥበቃ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡
- ከስርዓተምህዳር ውክልና በተጨማሪ የጥፍረ ረጂም ጡልጡሌ ዎፍና የአንገተ ነጭ ርግብ ለመጠበቅ ወካይ አካባቢ ነው፡፡

**ለ/ የብዛ-ህይወት ክምችት / Diversity/**

- የአካባቢውን የብዝሃ-ህይወት ሃብት ስንመለከት አሸንግድየ/ Kniphofia foliosa / በብዛት የሚገኝ ሲሆን እንዲሁም ቦታው ለጂብራና አስታን ለመጠበቅ ምቹ አካባቢ ሲሆን
- የቀይ ቀበሮና ታሪካዊ መኖሪያ አካባቢ ቢሆንም በዱር እንስሳት ላይ በአካባቢው ላይ እየደረሰ ባለው ተጽዕኖ ምክንያት ከአካባቢው ከጠፉች 100 ዓመት አስቆጥሯል፡፡
- ከፍተኛ ቦታዎች እንደ ደሴት ሆነው የብዝሃ-ህይወትንና ስርዓተ-ምህዳርን ስለሚይዙ የጮቄ አካባቢ የድንቅየና ብርቅየ የዱር እንስሳት መናኸሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡

**የአዕዋፍ መናኸሪያ መሆኑ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ብቻ የምትገኘውን**

Abyssinian Longclaw ***የያዘ በመሆኑ፡፡***

**በኢትዮጵያ ብቻ ይገኙ የነበሩና አሁን ኤርትራ የተጋራቻቸው የአዕዋፍ ዝርያዎች**

- ✓ *Wattled Ibis*
- ✓ *White-collared Pigeon*
- ✓ *Black-winged Lovebird*
- ✓ *Thick-billed Raven የሚገኙበት በመሆኑ፡፡*

- **በተደረገው ጥናት መሰረት ከ85 በላይ የዛፍና የሳር ዝርያዎችን መለየት የተቻለ ሲሆን በተለይም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ**

- *Acanthus sennii*
- *Echinops ellenbeckii*
- *Erythrina brucei*
- *Euryops pinifolius*
- Kniphofia foliosa
- *Lobelia rhynchopetalum*

**አቅፎ የያዘ ነው፡፡**

- **በአካባቢው ከ16 በላይ የሚሆኑ ታላላቅና ታናናሽ አጥቢዎች ተጠልለውበት እንደሚኖሩ በጥናት ወቅት የተረጋገጠ ሲሆን በአካባቢው ያለው የፍልፈልና የአይጥ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ አካባቢው ጥበቃ ቢደረግለት ወደፊት ቀይ ቀበሮን ወደ አከባቢው መስዶ እንደገና ማላመድ ያስችላል**

### ሐ/ ልዩ መገለጫ / Distinctiveness/

**የጮቄ ተፋሰስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የአባይ ፍሰት መጠን 9.5% /ይህም ከኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የአባይ ገባር ወንዞች 52839 ሚሊዮን ሜኩ ዓመታዊ ፍሰት ሲኖራቸው ከዚህም ውስጥ የጮቄ ገባር ወንዞች 5012 ሚሊዮን ሜኩ ፍሰት መጠን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ/ የያዘ ሲሆን ከጮቄ የሚነሱ ከ23 በላይ ዋና ዋና የአባይ ገባር ወንዞች ሲኖሩ የጮቄ የውሃ ማማነትን የሚያጎላው ሲሆን ከሌላዎች መሰል አካባቢዎች ጋር ሲነጻጸር የውሃ ምንጭነቱ ልዩ የሚያደርገው ሲሆን ይህን አካባቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አድረጎ ቢጠበቅ የታላቁን ህዳሴ ግድብ በዘላቂነት ጥቅም እንዲሰጥ ያስችላል፡፡/**

- **የጮቄ አካባቢ ከሌላዎች አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ የተሻለ የአስታ ሽፋን ያለው መሆኑ /የአባራ፣አባ ጂሜና ጎማዱር ጫካዎች/**
- **የጮቄ አካባቢ ከሌላዎች አካባቢዎች በተለየ ብዙ ቁጥር ያለው አንገተ-ነጭ ርግብ የሚገኝበት ቦታ ነው**

### መ/ ኢኮሎጂያዊ ጠቀሜታ /Ecological importance/

- **በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና በአካባቢው ያለው የአፍሮ አልፓይንና የሳብ አፍሮ አልፖይን ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል**
- **የዱር እንስሳት በአይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮአዊ አኗኗራቸዉ ይጠበቃሉ፣**

- ብርቅየ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና ከአካባቢቸዉ ጋር ሚዛናዊ ትስስር እንዲኖራቸዉ ያስችላል
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት በተፋሰሱ በተፈለገዉ ሁኔታ እንዲኖር ያስችላል

**ሠ/ በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን /Degree of interference/**

- ከባድ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር
- የጮቄውን የላይኛው አካል ለእርሻ አገልግሎት ማዋል /በጀብራ የተሸፈነውን አካባቢ ሳይቀር ለእርሻ አገልግሎት ማዋል/
- ደን ጭፍጨፋና ደን ቃጠሎ
- በጮቄው ክልል ውስጥ የቤት ግንባታ

**ረ/ የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Scientific and monitoring uses/**

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል በተለይም የደብረማርቆስና የባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች በቅርብ ርቀት ስለሚገኙ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል
- የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትንና በቤትና በዱር እንሰሳት መካከል ያሉ ተላላፊ የእንስሳት ስርጭት ለማወቅ ያስችላል
- ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለዉጥን መለካት ያስችላል
- የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሮአዊ እድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣዉን ለዉጥ ለመለየት ይረዳል

**ሰ/ የቦታ ስፋት /area size/**

ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታው በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ አንድ ሽህ ሄክታር መጠበቅ ይኖርበታል የሚለውን የ IUCN መስፈርት የሚያሟላና 17430 ሄ/ር ስፋት ያለው ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ሲሆን በአገራችን ውስጥ በአፍሮ ትሮፒካል ባዮም ክልል ውስጥ ከሚገኙ 49 የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 16 የአዕዋፍት ዝርያዎች በጮቄ ውስጥና በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) አስቀምጧል።

**ሸ/ ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/shape/**

ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል ። ሆኖም ግን የጮቄ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ከተራራው አናት ላይ በመቀነት መልክ የተዘረጋና ሾጣጣ በመሆኑና ከሁሉም አቅጣጫ ያለው ስፋት አነስተኛ በመሆኑ ለጥበቃ ምቹ አይደለም ለአካባቢ መጎሳቆልም በቀላሉ ተጠቂ ነው። ሆኖም ግን አካባቢው ተጋላጭ የሆነውን የአፍሮ-አልፓይን ስርተ ምህዳር አቅፎ በመያዙና ወሳኝ የሆነ የውሃ ማማ በመሆኑ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ አግኝቶ መጠበቅ ቢችል።

**ቀ/ በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች /Endemicity/**

**ከአዕዋፍ ዝርያዎች**

- **Abyssinian Longclaw**

**ከዕፅዋት ዝረያዎች ውስጥ**

- *Acanthus sennii*
- *Echinops ellenbeckii*
- *Erythrina brucei*
- *Euryops pinifolius*
- Kniphofia foliosa
- *Lobelia rhynchopetalum* ***ይገኝበታል***

❖ ከሀ-ቀ ያሉትን መስፈርቶች ስንመለከት የጮቄ አካባቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ ለመሆን ዝቅተኛውን መስፍርት የሚያሟላ ቢሆንም ቦታው ወደጥብቅ ስፍራነት መሸጋገር የሚችለው በአካር አካላት ሙሉ ተሳትፎ ዳር ድንበሩን በመከለል አሁን ያለበትን ከፍተኛ ጫና መቀነስ ሲቻል ነው። የቦታው ወደጥብቅ ስፍራነት መሸጋገር ከብዝሃ-ህይዎት ልማትና ጥበቃ ባሻገር ለታላቁ ህዳሴ ግድብ አጠቃቀም ዋስትና በመሆኑ ለውጤቱ የሁሉም አጋር አካላት ርብርብ ወሳኝ ነው።

## 13. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የጮቄ አካባቢ በርካታ ጠቀሜታ ያለዉና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀ የሚሰጣቸዉ ጠቀሜታዎች አካባቢያዊ፤ አገራዊና አለማቀፋዊ አሰተዋፆ ይኖራቸዋል። በተለይም ያለዉ የተፈጥሮ ሽፋንና መልካምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህይዎትና ተፈጥሮአዊ ገፅታ ከመጠበቅ

አልፎ የአለም ሙቀትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስና የአባይን ወንዝ የፍሰት መጠን በማስተካከልና የታላቁን የህዳሴ ግድብ ከደለል ለመጠበቅ የጎላ አስተዋጾ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የተፈጥሮ ደኑ የሚሰጠዉ ጠቀሜታ ከIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባቸዉ መስፈርት ሲነፃፀር ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጠዉ ሰንጠረዥ ያለዉ የተፈጥሮ ሀብትና የሚሰጠዉን ጠቀሜታ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባዉን ደረጃ ለመወሰን ያስችላል፡፡ ጥብቅ ስፍራ የመሆን መመዘኛዎችን ድምር ውጤት 77.75% ሲሆን አንድ ጥብቅ ስፍራ የታለመለትን አላማ ለማሳካት 75% ከዚያ በላይ መሆን ይገባዋል፡፡በመሆኑም ከተገኘው የጥናት ውጤት እና ቦታው የውሃ አናት በመሆን ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ሆኖ ቢጠበቅ

ሰንጠረዥ የጮቄ አካባቢ ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

| አቅም / ጠቀሜታ | ወካይነት | ብዝሃ ህይወት | ልዩ መገለጫ | ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ | በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን | የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ | የቦታ ስፋት/ ዙሪያ/ | ቅርፅ /መጠነ ድንቅየ ዝርያዎች | ደረጃ በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ዝ | ዝ | ከ | 77.8 |
| የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ | ዝ | ዝ | ዝ | ከ | ከ | ከ | ከ | ዝ | ከ | 55.6 |
| ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | 100 |
| ማህበራዊ ጠቀሜታ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ዝ | 88.9 |
| ሳይንሳዊ ጠቀሜታ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ከ | ዝ | ዝ | ከ | 77.8 |
| የመስህብነት ጠቀሜታ | ከ | ከ | ከ | ዝ | ከ | ከ | ከ | ዝ | ዝ | 66.7 |
| ደረጃ በ% | 83.3 | 83.3 | 83.3 | 83.3 | 100 | 100 | 66.6 | 33.3 | 66.6 | **77.75** |

መፍቻ ከ፡- ከፍተኛ 1-2 ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

አንድ የተፈጥሮ አካባቢ በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ ለመወሰን አካባቢው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን (Primary management objectives) በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል። ሠንጠረዥ ..... ላይ ማየት እንደሚቻለው የተፈጥሮ አካባቢው በደረጃ VI (protected area category VI) መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን በተራ ቁጥር 3፣4 እን 8 የተቀመጡትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል። ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ተሰጥቶት ማቋቋም ይቻላል። ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ በተፈጥሮ አካባቢው ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ድረስ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች (Primary management objective) የሚያሳካ ይሆናል።

## ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ

የጮቄ አካባቢ የAfrotropical highland biome የሚወክል ሲሆን በአፍሮ አልፓይንና ሳብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር ውስጥ የሚገኙትን የአስታ፣ጂባራ እና አሸንግድዬ የመሳሰሉት ዕፅዋትን እንዲሁም Afrotropical highland biome መጠለያቸው አድረገው የተቀመጡ 16 የአዕዋፍ ዝረያዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን የተለያዩ የአይጥና የፍልፈል ርያዎች አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህን አካባቢ በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት መጠበቅ በአፍሮ አልፓይንና ሳብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ ያስችላል።

**ሰንጠረዥ 2** Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)

| No. | Management categories | IUCN protected area categories | | | | | | | Total (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Ia | Ib | II | III | IV | V | VI | |
